# ደንብ

## የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)

ተዛማጅ መረጃዎች፦ CGA-RA፣ IED፣ IHC-RA፣ IKC-RA፣ IOE-RA፣ IOF-RA፣ JEB-RA፣ JEC-RA
ኃላፊ ጽ/ቤት፦ ዋና የአካዳሚ መኮንን

## ከ2ኛ ደረጃ ትምህርት ለመመረቅ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

I. ዓላማ

የሜሪላንድ ስቴት እና የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶችን (MCPS) ለመመረቂያ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን የአፈፃፀም ሂደት ለማሳወቅ።

II. ትርጉም፦

ሀ. የሚያሟላ/የምታሟላ ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ በዚህ ደምብ መሠረት፣ 18 ዓመት ወይም በላይ እድሜ ያለው (ያላት) ማለት ነዉ።

ለ. የሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ግምገማዎች (MHSAs) የሚባሉት በሜሪላንድ የትምህርት መምሪያ (MSDE) የሚዘጋጁ ወይም ተቀባይነት ያገኙ ፈተናዎች/ቴስቶች በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች ላይ ያተኮሩ የተማሪን ችሎታ እና እውቀት ለመለካት ደረጃ ጠብቀው የተዘጋጁ ናቸው። “MHSA” የሚለው ሀረግ የሚያካትተው ለሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተዘጋጀውን (HSA) ፈተና/ቴስት እና ለኮሌጅ እና ለሥራ ዝግጁነት ምዘና ትብብር ፕሮግራም (PARCC) የተዘጋጁ ቴስቶችን፣ እና ሌሎች በ MSDE ወደፊት የሚዘጋጁ ወይም ተቀባይነት የሚኖራቸዉን ጭምር ነው። ተማሪዎች የሚመለከታቸውን ኮርሶች ከጨረሱ በኋላ እነዚህን መመዘኛዎች/ፈተናዎች ይወስዳሉ።

ሐ. የሞንጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአካደሚ ማረጋገጫ የሽግግር ምዘና እቅድ (MHSA Bridge Plan for Academic Validation (Bridge Plan)) ተለይተው የሚታወቁ ተማሪዎች ከተለመደው ዓይነት ምዘና ይልቅ የ MHSA ተፈላጊ ነገሮችን ለሟሟላት እንዲወስዱ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) ያዘጋጀው አማራጭ ነው።

መ. የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ ዝርዝር መጽሔት በ MCPS የሚሰጡ ጠቅላላ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን በዝርዝር የሚገልጽ ዓመታዊ ህትመት ሲሆን እንዲሁም ደግሞ ለመመረቅ መሟላት ያለባቸውን ተፈላጊዎችን፣ ፈተናዎችን፣ ኢንተርንሽፖችን፣ ለሁለት ዓይነት ምዝገባ እድሎችን እና ስለ ልዩ ፕሮግራሞች ወቅታዊ መረጃዎችን ይገልፃል። የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ መጽሔት/ቡለቲን በየጊዜው እየተሻሻለ በተከታታይ ታትሞ ይሰራጫል። የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ እና ተሻሽለው የተጨመሩ ነገሮችም ታትመው በ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ ድረ-ገጽ ላይ ይወጣሉ።

ሠ. ዋና/የመጀመሪያ ክሬዲት የሚሰጠው ተማሪው(ዋ) አስቀድሞ የተመዘገበ(ች) ቢሆንም ክሬዲት ያላገኘባቸውን (ያላገኘችባቸውን) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን በተሟላ ሁኔታ ላጠናቀቀ(ች) ተማሪ ነው።

ረ. የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ማለት በተማሪው(ዋ) መሟላት ያለበት በት/ቤት ውስጥ ወይም ለማሕበረሰብ ለግለሰብ ወይም ለቡድን የት/ቤትን ወይም የማህበረሰብን ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ሥራው እና ሥራውን ስፖንሰር የሚያደርግ(ጉ) ግለሰብ/ቡድን በ MCPS ተቀባይነት ያገኙ መሆን አለባቸው።

ሰ. ክሬዲት ማዛወር ማለት ከ MCPS ውጭ/ሌላ ቦታ ቀድሞ ለወሰዳቸው(ለወሰደቻቸው) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች ተማሪው(ዋ) አዲስ በሚመዘገብበት (በምትመዘገብበት) የ MCPS ት/ቤት ርእሰ መምህር /ተወካይ ውሳኔ ለተማሪው(ዋ) የሚሰጥ ክሬዲት ነው። የሜሪላንድ ህጎች/ደንቦች ኮድ (COMAR) §13A.03.02.12 ተጨማሪ የዝውውር መመዘኛ፣ የተዛወረ/ች ተማሪን ከMHSA እና ተዛማጅ ኮርሶች ከግዴታ ነጻ የሙኖን መመዘኛን ጭምር ይደነግጋል።

III. **ሂደቶች/ቅደም-ተከተሎች**

*መግቢያ-ምደባ*

1. ተለዋጭ የ MCPS ፕሮግራም ካልተፈቀደ በስተቀር አንድ ተማሪ ከ8ኛ ክፍል በላይ የአራት ዓመት የፀደቀ ፕሮግራም ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለበት/አለባት። (ሰክሽን III.F. ላይ ስለ አራት ዓመት የምዝገባ አማራጮች ያገናዝቡ)

2. 8ኛ ክፍል የጨረሰ/ች አንድ/አንዲት ተማሪ የስቴት እና የአካባቢ ክሬዲት፣ ፈተናዎችን/ምዘናዎችን፣ እና የ SSL ተፈላጊዎችን ካሟላ/ች ከአራት ዓመት በላይ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪነት አይቀጥልም/አትቀጥልም።

3. በ 2014-2015 የትምህርት ዓመት ወይም በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘጠነኛ ክፍል ከገቡ ተማሪዎች ጀምሮ እያንዳንዱ በሜሪላንድ የሕዝብ ት/ቤት የሚማር/የምትማር ተማሪ በየዓመቱ ለአራት ዓመት የሂሳብ-ትምህርት ኮርስ መውሰድ አለበት/አለባት። የዚህ ተፈላጊነት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሂሳብ ኮርሶች ለተመዘገቡት አስፈላጊነቱ አይሥረዝላቸውም/ግዴታው ይመለከታቸዋል። እነዚህን አስፈላጊ የ MCPS ኮርሶች በየዓመቱ በ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት ላይ ይወጣል/ይታተማል። ሰክሽን III.C.3. ላይ እንደተገለጸው ተማሪዎች በጥንድ/በተጨማሪነት እየተማሩም ይህንን ተፈላጊ ሁኔታ ሊያሟሉ ይችላሉ።

B. በሞንጎመሪ ካውንቲ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተፈላጊ ሁኔታዎች ያሟሉ ተማሪዎች የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ይሸለማሉ። የMCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች ዕትም እና ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ጠቅላላ የስቴት እና የአካባቢ ለመመረቅ ተፈላጊ ሁኔታዎችን እንደየተማሪው/ዋ ሁኔታ በዘጠነኛ ክፍል የመጀመሪያ ዓመት ሊለያይ ይችላል።

1. ክሬዲት፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እና የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘና (MHSA) አስፈላጊ/ግዴታዎች፡-

    a) ክሬዲት/Credit

        (1) በሜሪላንድ ደንብ እና በሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ IED ላይ እንደተገለጸው፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርት ምህዳር እና መዋቅር ቢያንስ በስቴቱ ከሚፈለጉት ግዴታዎች በላይ ቦርዱ ለምረቃ የሚያስፈልጉ ልዩ ሁኔታዎችን ሊደነግግ ይችላል።

(a) በ MCPS 22 ክሬዲቶች ያስፈልጋሉ። ከነዚህም ውስጥ 19.5 ክሬዲቶች መገኘት ያለባቸው በእንግሊዝኛ፣ ማህበራዊ ጥናት፣ ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት፣ የጤና ትምህርት፣ ስነጥበብ፣ እና በቴክኖሎጂ ትምህርት በስኬታማነት በማጠናቀቅ ይሆናል።

(b) እያንዳንዱን መመዘኛዎች የሚያሟሉ የተወሰኑ ክሬዲቶች እና ኮርሶች በ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች መጽሔት ውስጥ በየዓመቱ ይታተማል።

(c) ተጨማሪ በምርጫ የሚወሰዱ/እሌክቲብ ክሬዲቶች በማናቸውም የሥርዓተ ትምህርት ዘርፍ ከሚቀርቡ ኮርሶች መምረጥ ይቻላል።

(2) ተማሪ ለመግባት የሚፈልግበት/የምትፈልግበት እያንዳንዱ የማህበረሰብ ኮሌጅ፣ ኮሌጅ፣ ወይም ዩንቨርስቲ MCPS ከሚጠይቀው የመመሪቂያ መስፈርቶች የተለየ የራሱን የመቀበያ/የማስገቢያ መመዘኛ/መስፈርት ሊመሰርት ይችላል። ስለ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ፕሮግራሞች ወይም ለመግባት የሚታሰቡ ት/ቤቶች ማናቸውም ተጨማሪ የመግቢያ መመዘኛዎች/መስፈርቶችን ተማሪዎች እና ወላጆቻቸው/ሞግዚቶቻቸው በንቃት እና በጥንቃቄ መመርመር አለባቸው።

(3) በክሬዲት/ያለክሬዲት ኮርሶች እና ተተኪ ውጤቶች

(a) በክሬዲት/ያለክሬዲት መጠቀም የሚቻለው በ MSDE ወይም MCPS በተለይ ለመመረቂያ የማያስፈልጉ ኮርሶች ላይ ነው። ለችሎታ ሠርተፊኬት ኮርስ (በሰክሽን/Section III.C ላይ የተጠቀሰውን የዲፕሎማ ድጋፍ ማረጋገጫዎችን ይመልከቱ) ክሬዲት/ያለክሬዲት ተግባራዊ አይደረግም።

(b) MCPS Regulation IKC-RA ላይ በተገለጸው መሠረት መተኪያ ውጤቶች በክፍል አማካይ ውጤቶች ላይ ይጨመራል የክፍል ውጤቶች አማካይ(GPA) እና የተመዘነ/ከፍተኛው የክፍል ውጤት አማካይ(WGPA) ላይ ይጨመራል።

b) የተማሪ አገልግሎት ትምህርት/Student Service Learning (SSL)

ተማሪዎች 75 ሰዓት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት/SSL ማጠናቀቅ አለባቸው። SSL ከበጎ ፈቃደኝነት ወይም ከማህበረሰብ አገልግሎት የሚለየው ተማሪዎች በትምህርት ቤት የተማሩትን በህይወት ተሞክሮ/በተጨባጭ የሥራ ዓለም ተግባራዊ በማድረግ የትምህርት ችሎታዎቻቸውን እንዲያሻሽሉ እድል ይሰጣል። በዚህም እነርሱ በትምህርታቸው እና በአገልግሎታቸው/ሥራ መካከል ያገኙትን ልምድ አፈፃፀም ላይ ያንፀባርቃሉ። የ SSL ተፈላጊ መስፈርቶች፣ ተቀባይነት ያለው የአገልግሎት እንቅስቃሴዎች፣ እና መዝገቦ የመያዝ ሂደት/record keeping procedures በ MCPS SSL ደረ-ገጽ ላይ ተገልጿል።

c) በሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች (MHSA)

ተማሪዎች በ MSDE የተደነገገውን የግምገማ አስፈላጊ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። ተማሪው/ዋ ወደ ኮርስ የገባ(ች)በት ዓመት ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪው/ዋ ወደ ዘጠነኛ ክፍል የገባ(ች)በት ዓመት ምክንያት የ MHSA ተፈላጊ መስፈርቶች ሊለያዩ ይችላሉ። እነዚህ ግምገማዎች በስቴት እና በአካባቢ ለምረቃ መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች በያዘዉ በ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ መጽሔት እና ተያያዥነት ያላቸዉ ተጨማሪዎች ውስጥ ይገኛል።

2. ለመመረቅ መስፈርቶችን ለማሟላት ክሬዲት ማዛወር/ማስተላለፍ

a) ከ MCPS ውጪ ማስተላለፍ/ማዛወር

(1) አንድ ተማሪ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለመሸለም የሚችለው/የምትችለው፣ ተማሪው/ዋ ከሌሎች መመረቂያ መመዘኛዎች በተጨማሪ በሜሪላንድ የህዝብ ት/ቤት ከመመረቂያ ወቅት ቀድሞ ባለው አንድ ሙሉ ሴሚስተር መከታተል ከቻለ/ች ብቻ ነው።

(2) ተቀባይነት ያለው የህዝብ ት/ቤት ያልሆነ ወይም ከካውንቲ ውጭ ት/ቤቶችን ክሬዲት በርእሰ መምህር/ት ተቀባይነት ማግኘት እና ወደ MCPS ክሬዲት ተመጣጣኝ የኮርስ ሥራዎች መቀየር አለበት።

(3) ከዩ.ኤስ ውጪ የተገኙ ክሬዲቶችን ለማዛወር በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ ጽ/ቤት የዓለም አቀፍ ቅበላ እና ምደባ/ምዝገባ ክፍል/MCPS International Admissions and Enrollment unit in the Office of Student and Family Support and Engagement ጋር በመመካከር ርእሰ መምህሩ/ሯ ይወስናል/ትወስናለች።

(4) የ SSL ተፈላጊ መስፈርት በተመዛዛኝ የሚያዘው/የሚታሰበው ለመጀመሪያ ጊዜ ከ6ኛ ክፍል በላይ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች ነው።

(5) የህዝብ ት/ቤቶች ካልሆኑ ወይም ከስቴት ውጪ ከሆኑ ት/ቤቶች የሚዛወሩ ተማሪዎች በ COMAR በተገለጹት ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት አንድ ወይም የበለጠ የ MHSA ግዴታ ሊቀር/ሊሰረዝላቸው ይችላል።

(a) የህዝብ ካልሆኑ ት/ቤቶች ወይም ከስቴት ውጪ ከሆኑ ት/ቤቶች የሲንየር ዓመታቸውን የመጀመሪያ ሴምስተር ጨርሰው ወደ MCPS የሚዛወሩ ተማሪዎች የ MHSA መስፈርት-ግዴታ ይሠረዝላቸዋል።

(b) ቢሆንም ግን፣ እንዲህ ዓይነት ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጊዜያቸው በሜሪላንድ የህዝብ ት/ቤት ተምረው ከሆነ፣ በሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለተማሩበት ወቅት የ MHSAን መሥፈርት ማሟላት ይጠበቅባቸው ይሆናል።

(c) በሚቀበለው/በምትቀበለው ርእሰመምህር ጥያቄ፣ በ COMAR ድንጋጌ መሠረት ርእሰመምህሩ/ሯ ያጸደቀ(ች)ውን የዝውውር ክሬዲት/ክሬዲቶች ተማሪው/ዋ አንድ ወይም የበለጠ የ MHSA ተፈላጊ መስፈርቶች ይታለፍለ(ላ)ት እንደሆነ የጋራ ኃላፊነት ጽ/ቤት (OSA) ይገመግማል።

(6) በሲንየር ዓመት ላይ ሆነው ወደ MCPS የገቡ ተማሪዎች በቦርድ ፐሊሲ/Board Policy IED የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የትምህርት መዋቅር ላይ እንደተደነገገው፣ ቢያንስ በስቴት ደረጃ ለመመረቅ ማሟላት ከሚገባቸው በላይ ሌሎች የመመረቂያ መስፈርቶች ይታለፍላቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች በ MSDE ከተደነገገው የምረቃ መስፈርቶች ያለፈ በ MCPS ተፈላጊ ተጨማሪ የሂሳብ ክሬዲት እና በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ግማሽ ክሬዲት ይታለፍላቸዋል።

(7) ተማሪዎች በሲንየር ዓመታቸው የመጨረሻ ሴሚስተር ላይ ከአንድ የሜሪላንድ የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወደ ሌላ የሜሪላንድ የህዝብ ት/ቤት የተዛወሩ እንደሆነ እና ለምረቃ መሟላት ያለባቸው ሁሉ ተሟልቶ ከሆነ፣ በርእሰ መምህሩ/ሯ ስምምነት፣ ወይም ከአንድ በላይ የአካባቢ ትምህርት ሥርአት ያለበት ከሆነ የአካባቢ ትምህርት ዋና ኃላፊዎች/superintendents ከተስማሙ ከሁለቱ በአንደኛው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቅ ይችላል/ትችላለች።

3. በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጡ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች

a) የሥርዓተ ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞች ጽ/ቤት (OCIP) ተባባሪ ሱፐርኢንተንዳንት የትምህርት ዋና መኮንን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ክሬዲት የሚያስገኙ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መሰጠት ያለባቸውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን፣ ባሉት ፕሮግራሞች እና መገልገያዎች ላይ ምን ዓይነት ተፅእኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ከገመገሙ በኋላ፣ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው መምህራን ማግኘት መቻሉ ታሳቢ ተደርጎ ለመወሰን ይችላሉ። OCIP በትምህርት ሥርዓቱ ተግባራዊ ከመደረጉ አስቀድሞ አነስተኛ ቁጥር ባላቸው ት/ቤቶች ውስጥ የናሙና ጥናቶችን ያካሄዳል።

b) የሚከተሉት መስፈርቶች በጠቅላላ ከተሟሉ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቂያ ክሬዲት ማግኘት ይቻላል፦

(1) ተማሪው/ዋ የአካባቢ ት/ቤትን ሥርዓተ ትምህርት ዓላማ በማሟላት/በመፈጸም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ ወስዷል/ወስዳለች።

(2) መምህሩ/ሯ የኮርሱን እና ለሚያስተምረው/ለምታስተምረው የትምህርት ኮድ ሠርተፊኬትና አስፈላጊ ነገሮችን ያሟላል/ታሟላለች።

(3) የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ተሰጥቷል።

(4) የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎችም ልክ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ተመሣሣይ መስፈርቶችን ማሟላት እና የመጨረሻ ውጤት A፣ B፣ C፣ ወይም D ማግኘት አለባቸው።

5) በተለይ ለምረቃ አስፈላጊ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ለክሬዲት ከተሰጠ፣ ተማሪዎች የተደራጀዉን/የተመሰረተዉን የኮርሶች ቅደም ተከተል መከተል አለባቸው።

C. ክሬዲት ለማግኘት አማራጭ አቅርቦቶች

1. ከትምህርት ቀናት ውጪ የሚሰጡ የ MCPS ኮርሶች

a) ተማሪዎች ከመደበኛው የትምህርት ቀናት ወይም ከመደበኛ የትምህርት ዓመት ውጪ በ MCPS የሚሰጡ የትምህርት ዕድሎችን በመጠቀም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለማግኘት ይችላሉ።

b) ስለ ኮርሱ ኃላፊነት ያለው የ MCPS አስተዳዳሪ ተማሪው/ዋ ያገኘ(ች)ውን ደረጃ እና ጠቅላላ ክሬዲቶችን ለተማሪው/ዋ የአካባቢ ት/ቤት ሬጅስትራር ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ከመደበኛ የትምህርት ቀናት ውጪ በ MCPS ኮርሶች የተገኙ ውጤቶች የተመዘነ እና ያልተመዘነ/weighted and unweighted የክፍል ነጥብ አማካይ ስሌት ዉስጥ ይካተታሉ።

c) ተፈላጊ የሆኑ ክሬዲቶችን በማሟላት ከ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በሰመር ፕሮግራም ለመመረቅ የሚፈልጉ ተማሪዎች በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ደንብ/MCPS Regulation CGA-RA ላይ የተገለጹትን ቅድመሁኔታዎች እንዲያሟሉ ይጠበቃልየሰመር ት/ቤት ፕሮግራም

2. ከ MCPS ውጪ በሌሎች ተቋማት የሚሰጥ ክሬዲት

a) ከ MCPS ውጪ ባሉ ተቋማት ክሬዲት ኖሯቸው ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መመረቂያ ኮርሶች ለማሟላት የሚያመለክቱ ተማሪዎች ለኮርስ ከመመዝገባቸው አስቀድሞ የርእሰ መምህር ይሁንታ/approval እንደሚከተለዉ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡-

(1) የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህር ይሁንታ/approval ያገኛሉ።

(2) ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አነስተኛ እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ይሁንታ/approval ማግኘት ያለባቸው ትምህርት ከሚከታተሉበት አካባቢ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህር ነው።

b) ለኮርስ ሥራ የርእሰመምህር ይሁንታ/approval፣ በሰክሽን III.C.3 ላይ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ለተጣማጅ ትምህርት ምዝገባ/dual enrollment በሚከተሉት ላይ የተሞረኮዘ ይሆናል፡-

(1) ኮርሱ በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ሥርዓተ ትምህርት/MCPS curriculum ላይ ስለሌለ ለተማሪው አይገኝም፣ ተማሪው/ዋ በተማረበት/በተማረችበት ትምህርት ቤት አይሰጥም፣ ወይም ከተማሪው/ዋ የጊዜ ሰሌዳ ጋር አይገጣጠምም።

(2) ከ MCPS ኮርስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለማግኘት፣ ተማሪው/ዋ ኮርሱ መሆኑን ማሳየት/ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት፣

(a) ለተማሪው/ዋ ሁሉንም ደረጃ የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ/ኮርሶችን ሙሉ እውቀት/ችሎታ ኖሮ(ሯ)ት ለማጠናቀቅ እድል የሚሰጥ ከሆነ፣

(b) በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የሚሰጠውን ጥብቅ መርሃ-ትምህርት/MCPS syllabus ይመጥናል ወይም ይበልጣል፣ እና

(c) በ MSDE የተደነገጉ ማናቸውንም ተፈላጊ ሁኔታዎች ያሟላል።

(3) ኮርስ ሰጪው እውቅና ባለው ኤጀንሲ የፀደቀና በ MSDE እና በ MCPS ተቀባይነት ያገኘ መሆን አለበት፣ እናም ኮርሱ በ MCPS መፅደቅ አለበት።

(4) በሜሪላንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ በጥንድ የሚማሩ ተማሪዎች ካልሆነ ከዚህ በታች በሰክሽን III.C.3 እንደተገለፀው እና ከታወቀው አሠራር በስተቀር ከመደበኛው የትምህርት ቀናት ወይም የትምህርት ዓመት ውጪ ለሚወሰዱ ኮርሶች ክፍያ ወጪዎችን MCPS አይሸፍንም ወይም አስተዋጾ አያደርግም።

3. ሁለትዮሻዊ ምዝገባ

a) የ MCPS ተማሪዎች ሆነው እያለ፣ የተወሰኑ መስፈርቶችን እስካሟሉ ድረስ ተማሪዎች በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና/ወይም ለኮሌጅ ክሬዲት ኍለትዮሽ ምዝገባ ሊገቡ/ሊመዘገቡ ይችላሉ። ቢሆንም ተማሪዎች በኮሌጅ ደረጃ ኮርሶች በአንድ ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የኮሌጅ ክሬዲት ሊያገኙ የሚችሉበት እና ተማሪዎች የኮሌጅ ክሬዲት ብቻ የሚያገኙትበት እንደሚከተለው ልዩነት አላቸው:-

(1) ሁለትዮች ምዝገባ/ምደባ ማለት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና የኮሌጅ የሁለቱንም ክሬዲት ያገኛሉ ማለት ነው።

(2) በአንድ ዓይነት ምዝገባ(ምደባ) Concurrent enrollment ማለት ተማሪዎች በኮሌጅ ትራንስክሪፕታቸው ላይ የኮሌጅ ክሬዲት ብቻ ያገኛሉ ማለት ነው።

b) ስለ ሁለትዮሽ ምዝገባ ወይም ስለ አንድ ጊዜ ምዝገባ ስለ ማመልከቻዎች እና የበለጠ መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ተማሪዎች በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአካደሚ አማካሪዎቻቸውን ወይም ካውንስለሮቻቸውን ስለሁለትዮሹ ምዝገባ ፕሮግራም ድጋፍ እንዲያማክሩ ያስፈልጋል።

c) ስለ ሁለትዮሽ ምዝገባ ዓላማዎች የሚከተለው ተፈጻሚ ይደረጋል:-

(1) ለእያንዳንዱ የ3-ወይም-የ4 ክሬዲት የኮሌጅ-ደረጃ ኮርስ በስኬታማነት በማጠናቀቅ ለመመረቅ የ 22-ክሬዲት አስፈላጊነት ለማሟላት በቅድሚያ ከፀደቀ፣ ተማሪው/ዋ 1.0 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ያገኛል/ታገኛለች። (ከአራት ክሬዲት በላይ ዋጋ ስለሚኖራቸው የኮሌጅ ኮርሶች ተገቢውን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት በሚመለከት ርእሰመምህራን ከተባባሪ የ OCIP ሱፐር ኢንተንዳንት/ተወካይ ጋር መነጋገር/ማማከር ይኖርባቸዋል)።

(2) ሁለትዮሽ የተመዘገቡ ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት የኮሌጅ ኮርሶችን በድጋሚ ለመውሰድ አይችሉም፣ እና የመጀመሪያውን የኮሌጅ ኮርስ ካላለፉ/ከወደቁ ወይም ሳይፀድቅላቸው ጥለው ከወጡ፣ ሌሎች የኮሌጅ ኮርሶችን ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክሬዲት ለመውሰድ አይችሉም።

(3) በሜሪላንድ ህግ እንደተደነገገውና ከ MCPS ጋር ባለው የጋራ ስምምነቶች መሠረት፣ በሜሪላንድ ስቴት የህዝብ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለተዮሻዊ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች እና በስቴቱ የህዝብ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የሜሪላንድ የማህበረሰብ ኮሌጆች እና የሜሪላንድ የአራት-ዓመት ዩንቨርስቲዎችን ጨምሮ፣ ለመማሪያ ክፍያ ቅናሽ የማግኘት እድል ብቃት ይኖራቸው ይሆናል።

d) በቅድሚያ ሳይፀድቅላቸው የኮሌጅ ትምህርት በመውሰድ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች፣ ወይም ወደ MCPS ከሌላ ኮሌጅ ክሬዲት ይዘው የሚዛወሩ ወይም በትራንስክሪፕታቸው ላይ ቀደም ሲል ከተዛወሩበት ት/ቤት ክሬዲት ያልተመዘገበላቸው ተማሪዎች ሁለትዮሻዊ ምዝገባ ለማግኘት የሚችሉት በእያንዳንዱ ጉዳይ ተሞርኩዞ በርእሰ መምህር እና የ OCIP ተባባሪ ሱፐር ኢንተንደንት/ተወካይ አማካኝነት ሲፀድቅ ብቻ ነው።

4. የኮርስ ክሬዲት ዋጋ፣ ምዘና/weight፣ እና የዲፕሎማ አሰጣጥ ሂደት

a) ከላይ ሰክሽን III.C.2 እና 3 ላይ እንደተገለጸው፣ ከ MCPS ውጪ ባሉት ተቋማት የተገኙ የኮርስ ክሬዲቶች ተማሪው/ዋ በኮርሱ ከመመዝገቡ/ቧ አስቀድሞ ባለክሬዲት/ያለክሬዲት በማለት ምርጫ ካላደረገ/ች በስተቀር በተማሪው/ዋ የተመዘነ/ያልተመዘነ (weighted and unweighted) የክፍል ነጥብ አማካይ ውጤት ላይ ይጨመራሉ።

b) ኮርሱ በርእሰመምህር አማካይነት የላቀ ወይም እንደ ከፍተኛ ደረጃ ኮርስ ተደርጎ ከተወሰደ እና የኮርሱ ኮድ/መለያ የጥራት ነጥብ የማያካትት ከሆነ፣ አማካይ የነጥብ ውጤቱ በ A፣ B፣ C፣ ወይም D ውጤት ላይ አንዳንድ የጥራት ነጥብ እየተጨመረ የተመዘነ የክፍል ነጥብ አማካይ ውጤት ይሰላል።

c) በሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች/MCPS Regulation IKC-RA ደንብ ላይ በተገለጸው መሠረት ለኮርሱ የተሰጠውን ውጤት/The course grade በማመዛዘን Grade Point Averages(GPA) እና Weighted Grade Point Averages (WGPA) ስሌት ውስጥ ይካተታል።

d) ከ MCPS ውጪ ባሉ ተቋማት ለምረቃ ተፈላጊዎቹን መስፈርቶች አሟልተው ከጨረሱ በኋላ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ለማግኘት የሚያስቡ ተማሪዎች የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

(1) ከ MCPS ውጪ ለመመረቅ የሚያበቁ ኮርሶችን ለማጠናቀቅ ያላቸው እቅድ አስቀድሞ በአካባቢ ት/ቤት ርእሰ መምህር በጽሑፍ መፅደቅ ይኖርበታል።

(2) ኮርሱን የሚሰጠው የትምህርት ተቋም ክሬዲት እና/ወይም ዲፕሎማ ከመሰጠቱ በፊት ተማሪው(ዋ) በኮርሱ ላይ ያገኘውን/ያገኘችውን ውጤት ሪፖርት ማድረግ አለበት።

(3) ዲፕሎማዎቹ የሚሰጡት በአካባቢ ት/ቤት ስም ስለሆነ የዚያን ት/ቤት ርእሰመምህር ፊርማ ሊኖረው ይገባል።

D. ከት/ቤት ውጪ ከሥራ ጋር የተገናኙ ልምዶች

1. ከት/ቤት ውጪ በክፍያም ይሁን ያለክፍያ የሥራ-ልምድ ክሬዲት ለማግኘት፣ ተማሪው/ዋ በቅድሚያ አግባብነት ባለው የ MCPS ኮርስ መግባት አለበ(ባ)ት (ለምሳሌ፦ ኢንተርንሺፕ ወይም በ MCPS የተመዘገበ የመስክ-ሥራ ልምድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መጽሔት/መግለጫ፣ ከመስኩ ጋር የተገናኘ ቁጥጥርና መመሪያ ያካትታል።

2. ለእንደዚህ ዓይነት የ MCPS ቁጥጥር ያለው እና የፀደቀ ከት/ቤት ውጪ ለሚደረግ የሥራ ወይም የሙሥክ ልምምድ፣ መመረቂያ መስፈርት ለማሟላት ለአንድ ተማሪ ከዘጠኝ በምርጫ ከሚወሰዱ ክሬዲቶች በላይ ላይሰጥ ይችላል።

E. የግል-የተናጠል ትምህርት/ጥናት

1. የግል-የተናጠል ትምህርት/ጥናት ተማሪዎች ከዓላማዎች፣ ግቦች፣ ወይም ከደረጃ የሚያልፍ ስኬታማነት ላይ ለመድረስ ወይም ከዚያም ለማለፍ የሚያስችላቸውን የትምህርት ልምዶችን እድል ይሰጣል። የግል-የተናጠል ትምህርት/ጥናት እድሎችን ለማግኘት የሚያስችሉ መስፈርቶች የሚዘጋጁት በት/ቤት ባለሙያ ሠራተኞች ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ተማሪዎች እና ወላጆች/ሞግዚቶች ይሳተፉበታል።

   a) እነዚህ ልምምዶች በአካባቢው ት/ቤት መደበኛ የመማሪያ ክፍሎች ያልተሟሉ/የሌሉ የትምህርት ይዘት፣ ማቴሪያሎችን እና ባለሙያ ሰዎችን ለማግኘት ያስችላሉ።

   b) የግል-የተናጠል ትምህርት/ጥናት እንደየኮርሱ ሁኔታ ከበርካታ ሳምንታት እስከ ሴሚስተር ወይም ከዚያም የሚረዝም ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

   c) የመመረቂያ መስፈርቶችን ለማሟላት አንድ ተማሪ ከአራት ክሬዲቶች የበለጠ የግል-የተናጠል ትምህርት/ጥናት ላይሰጠው/ላይሰጣት ይችላል።

2. ከሙያ ሠራተኞች ጋር በመተባበር፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ የሚከተሉትን ሥርዓቶች እንዲሟሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት/አለባት።

   a) ለተማሪዎች የግል-የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም የትምህርት ቤት ልምምድ አካል መሆኑን ለሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ለሠራተኞች ማሳወቅ፣

   b) ተማሪዎች ለግል-የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም በፍላጎት ለመሳተፍ የሚያቀርቧቸውን ማመልከቻዎች የአቀራረባቸውን ቅደም-ተከተልና የሠራተኞችንና የባጀት መኖር-ያለመኖር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ማጽደቅ/ያለማጽደቅ

   c) መመርመር፣ ማፅደቅ፣ እና ፕሮጀክቶችን በተናጠል መገምገም

   d) ከት/ቤት ሕንፃ ውጪ ለማጥናት/ለመማር የቀረቡትን ጥያቄዎች በሙሉ ወይም በከፊል ለማከናወን መፍቀድ/አለመፍቀድ (ለማፅደቅ የ MCPS ቅጽ 560-31 መሞላት አለበት MCPS መጓጓዣ/ትራንስፖርት ስለማይሰጥ ወላጅ/ሞግዚት ትራንስፖርት ለማቅረብ መስማማት አለባቸው)

   e) ከትምህርት ቤት ርቆ የግል-የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ለመካፈል ተማሪው/ዋ

ከወላጅ/ሞግዚት ወይም እድሜ ከሚፈቅድ ተማሪ የጽሑፍ ፈቃድ ማቅረብ አለበት/አለባት።

3. የግል-የተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ሲዘጋጅ፣ ት/ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማህበረሰቡን መጠቀሚያዎች/resources መገልገል አለበት።

4. ተማሪዎች በአግባቡ የሙያ ሠርተፊኬት ያለው መምህር ጋር በመተባበር እና በትክክል ሙያውን የተካነ ሰርተፊኬት ባለው መምህር ቁጥጥር እንደሚማር/እንደምትማር ማስረጃ ለማቅረብ ከወላጆች/ሞግዚቶችጋር በመተባበር ለራሳቸው የግል-ተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ተነሳሽነትና እቅድ ሃላፊነት አለባቸው።

5. መምህሩ/ሯ ተማሪው/ዋ በኮርሱ ዓላማዎች፣ግቦች፣ ወይም ደረጃ የጠበቀ እውቀት መጨበጡን/መጨበጧን በመገምገም ተገቢውን የኮርስ ውጤት እና ክሬዲት በመስጠት ወደ ርእሰመምህር የማሳለፍ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

6. የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ክትትል ሪኮርድ ማድረጊያ ዘዴ ተዘጋጅቶ የግል-ተናጠል ትምህርት ፕሮግራም ለመከታተል የተመዘገቡበትን ጊዜያት በትክክል "በትምህርት ገበታ ላይ መገኘታቸውን" ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

F. አራት-ዓመት ለመግባት አማራጮች

ሌላ አማራጭ የትምህርት እቅድ ካልተነደፈ ወይም እንዲዘለል የተፈቀደ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ከ8ኛ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የአራት ዓመት ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።

1. ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት የማስቀረት ሁኔታ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል።

   a) ተማሪው/ዋ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመመረቁ(ቋ) አስቀድሞ እውቅና ባለው ኮሌጅ ተቀብለው(ዋ)ት ከሆነ።
   b) ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ምረቃ በፊት ተማሪው/ዋ ለተፈቀደለ(ላ)ት የሙያ/ቮኬሽናል፣ ቴክኒካዊ፣ ወይም ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራም ለመግባት ተቀባይነት ያገኘ/ች።

   c) ተማሪው/ዋ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የገባ(ች)ው የክፍል ተማሪዎች ካላቸው እድሜ ከፍ ብሎ/ላ ባለው/ባላት የእድሜ ቅደም-ተከተል ከሆነ።

   d) ተማሪው/ዋ ሁሉንም የመመረቂያ መስፈርቶች ካጠናቀቀ/ች።

2. በፈተና የሚሰጥ ክሬዲት

   አልጀብራ 2 ወይም እንግሊዝኛ 12 በስተቀር (በሁለቱም ሳይሆን) ሁሉንም ለመመረቅ የሚያስችሉ መስፈርቶችን ያሟሉትን ተማሪዎች ስቴቱ ባፀደቀው ፈተና እና በ MSDE በተገለፀው መሠረት ማለፊያ ውጤት አግኝተው ክሬዲት እንዲያገኙ MSDE ይፈቅዳል።

3. ሌላ አማራጭ የምዝገባ ሂደቶችን እቅድ ለማዳበር እና ማስቀረት/ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍን የማጽደቅ ሂደት/ፕሮሲጀር እንደሚከተለው ይሆናል።

a) ብቃት ያለው ተማሪ ወይም ወላጅ/ሞግዚት የ MCPS ቅጽ 280-97 ማግኘትና መሙላት፣ ለአራተኛ ዓመት የመግቢያ ተፈላጊ መስፈርቶችን ለማስቀረትእና ቅጹን ለት/ቤት ካውንስለር ከወቅታዊ የ MCPS ቅጽ 560-45 ማቅረብ፣የተማሪ የትምህርትና የእቅድ ሥራ ሠንጠረዥ በአንድ ፕሮግራም ወይም ኮርስ ለመግባት ከታሰበው ቢያንስ አንድ ሙሉ ሴሚስተር ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች በቂ ጊዜ በመስጠት።

b) ስለታሰበው ፕሮግራም የት/ቤቱ ካውንስለር ከተማሪው/ዋ፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ጋር ለመነጋገር የስብሰባ ጊዜ ቀጠሮ ይይዛል/ትይዛለች። የት/ቤት ካውንስለር አስተያየታቸውን ወደ ርእሰ መምህር ያስተላልፋል/ታስተላልፋለች። ኮሌጅ፣ ቮኬሽናል/የሙያ ትምህርት፣ የቴክኒክ፣ ወይም ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተቀባይነት ወዳለው ተቋም ለመግባት እንዲችል/እንድትችል እንዲፀድቅ አስተያየት ሊወሰን ይችላል።

c) የሱፐር ኢንተንደንት ተወካይ እንደመሆኑ/ኗ መጠን ርእሰመምህሩ/ሯ በማፅደቅ ወይም ባለማፅደቅ የ MCPS ቅጽ 280-97 ቅጺውን አራተኛ ዓመት ለመቀጠል ተፈላጊው መስፈርት እንዲታለፍ የቀረበውን ጥያቄ የመጨረሻውን ውሳኔ ለተማሪው፣ እና ለወላጅ/ሞግዚት በመግለጽ።

G. የዲፕሎማ ማረጋገጫዎች

የከፍተኛ ችሎታ/የሽልማት ሠርተፊኬት

የሽልማት የሚገባው/ት አገልግሎት ሠርተፊኬት ማለት 260 ወይም የበለጠ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት/SSL ሰዓታትን ለተሳተፉ ተማሪዎች ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ጋር የሚሰጥ የ MCPS ሠርተፊኬት ነው። በምረቃ ወቅት ለተመራቂዎች ሽልማትና ልዩ እውቅና የሚያሰጥ አገልግሎት ይሰያል።

2. የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የከፍተኛ ችሎታ ሠርተፊኬት

የMCPS ከፍተኛ ችሎታ ሠርተፊኬት የሚከተሉትን ተጨማሪ አገልግሎቶች በስኬታማነት/በጥሩ ውጤት ሲያጠናቅቁ ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ ማረጋገጫ ጋር የሚሰጥ ሰርተፊኬት ነው።

a) 3.0 አማካይ ከፍተኛ ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ያለው/ያላት፣

b) የ MCPS አልጄብራ/Algebra 2 ኮርስ ክሬዲት ያገኘ/ያገኘች፣

c) በ MCPS የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርስ መግለጫ ላይ ጠንከራ ተብለው የተመደቡ ኮርሶች ላይ ቢያንስ 12 ክሬዲት ያገኘ/ያገኘች፣

3. የሜሪላንድ የመድብለ ቋንቋ መለያ

የሜሪላንድ የመድብለ ቋንቋ መለያ ማለት በከፍተኛ ደረጃ መስማት/ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ እና በመጻፍ ከእንግሊዝኛ ሌላ/ተጨማሪ አንድ ወይም የበለጠ ቋንቋዎችን ለሚችሉ ተማሪዎች

ሽልማት እንዲሰጥ በሜሪላንድ ህግ የተፈቀደ እውቅና መስጠት ነው።

a) የሜሪላንድ የመድብለ ቋንቋ መለያ የተመሠረተው በቋንቋ ትምህርት ጥብቅ የችሎታ ምዘና ያለፉትን እውቅና ለመስጠት እና ስለ ከፍተኛ ችሎታቸው ሽልማት ለመስጠት ነው።

b) MSDE የብቃት መስፈርቶችን እና ለእነዚያ መስፈርቶች የብቃት መመዘኛ ፈተና/መለኪያ ያዘጋጃል።

c) የዲፕሎማ ማረጋገጫው ለ MCPS ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን በ2017 እና ከዚያ በኋላ ከ MCPS ለሚመረቁ ይሰጣል።

H. የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት

የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ስንክልና ያላቸው እና የዲፕሎማ መስፈርቶችን ለማሟላት የማይችሉ፣ ነገር ግን ከዚህ በታች የተገለጹትን በሜሪላንድ ህግ የተቀመጠ የስቴት ድንጋጌዎችን ለሚያሟሉ ተማሪዎች የሚሰጥ ሠርተፊኬት ነው።

1. የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ተማሪው/ዋ ወደ ተለዋጭ የትምህርት ውጤቶች እንደሚገመገም MCPS Curriculum 2.0 ትምህርት መግባት እንዳለበ(ባ)ት፣ ምዘና እንደሚደረግ፣ እና የማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት እስከሚወስን ድረስ ለሁሉም ተማሪዎች እንደ ዲፕሎማ ተማሪ ይቆጠራሉ፣ ይገመገማሉም ውጤትም ይሰጣል። Annotated Code of Maryland, Education Article, § 8-405(f) ላይ ከተገለጸው በስተቀር፣ እንዲህ ዓይነቱ ቆራጥ ውሳኔ ከወላጅ/ሞግዚት በጽሑፍ የተረጋገጠ ስምምነት ያስፈልገዋል።

2. ተማሪው/ዋ ከ8ኛ ክፍል በላይ ቢያንስ ለአራት ዓመት የትምህርት ፕሮግራም እየተከታተለ/እየተከታተለች ሳለ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም IEP ቡድን ከተማሪው/ዋ እና በወላጆች/ሞግዚቶች ስምምነት ግለሰቡ(ቧ) ወደ ትክክለኛው የሥራ ዓለም በመግባት፣ ሃላፊነት የሚሰማ(ት)ው ዜጋ፣ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በተደሳችነት ህይወቱ(ቷ)ን እንዲ(ድት)መራ ለማስቻል የሚያስችለው/የሚያስችላት እውቀት እንዲያገለብት/እንድታገለብት ነገር ግን በዚህ ያልተገደበ፡-

   a) ጠቃሚ ሥራ፣

   b) ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ስልጠና፣

   c) የሥራ ቅጥር ድጋፍ፣ እና

   d) ሌሎች ከማህበረሰቡ ጋር የተዋሃዱ አገልግሎቶች።

3. ተማሪው/ዋ ከ 8ኛ ክፍል በላይ ለአራት ዓመት ወይም ከእድሜው/ዋ ጋር ለሚመጥን የትምህርት ፕሮግራም ገብቷል/ገብታለች እና በዚህ የትምህርት ዓመት ማለቂያ ላይ 21 ዓመት ይሞላዋል/ይሆናታል።

4. የተማሪው(ዋ)ን የሙያ ትምህርት/እውቀት የሚገልጽ የመሰናበቻ ሠነድ ከሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ጋር አባሪ መደረግ አለበት።

5. ተማሪው/ዋ የመጨረሻውን የትምህርት ዓመት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት ስንክልና ላለበ(ባ)ት ተማሪ የሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቂያ ሠርተፊኬት ፕሮግራም ውሳኔ አይሰጥም።

6. ከባድ የመረዳት ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ ለሜሪላንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዲፕሎማ መመረቂያ መስፈርቶችን አያሟላም/አታሟላም ይሆናል፣ ተማሪው(ዋ)

    a) በአማራጭ አካደሚ ክንውን ደረጃ በአማራጭ የምዘና ፕሮግራም ከተሳተፈ/ች፣ እና

    b) የአማራጭ ትምህርት ክንውን ደረጃ በመጠበቅ በአማራጭ የአካደሚ ትምህርት በሁለተኛ ደረጃ እስከሚጨርስ/እስከምትጨርስ ከቀጠለ/ች።

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች/Related Sources:**

Annotated Code of Maryland, Education Article §7-103, §7-205, §8-405(f). §18-14A-01, §18-14A-04; Code of Maryland Regulations (COMAR) §13A.03.02 et seq., §13A.07.03.01-.05, and §13B.07.02.01C; Montgomery County Public Schools High School Course Bulletin and associated addenda

**Regulation History:** Formerly Regulation No 310-3, March 22, 1976; revised December 1986; revised May 17, 1988; revised July 20, 1994; revised July 23, 1997; revised May 14, 2008; revised February 14, 2011; revised July 1, 2013; revised July 26, 2017; revised October 24, 2017.